# ገቢያችን ህልውናችን

14ኛ ዓመት | ቁጥር 168 | ታኅሣሥ 2016 ዓ.ም | በነፃ የሚታደል

## በውስጥ ገፆቻችን




«የደረሰኝ አሰጣጥ ችግር የሚጀምረው ከአዲስ አበባ/መርካቶ ነው»

ገጽ 3



የ150 ኪሎ ግራም ዱቄት ገንፎ

ገጽ 5


# የማያስጥል ዝነኝነት



ሰዎች፤ በፊልም፣ በሙዚቃ፣ በድምጻዊነት፣ በጋዜጠኝነት እና በሌሎችም የጥበብ ሥራዎች፣ በስፖርት፣ በፖለቲካ፣ በንግድ እና ታዋቂነትን ባተረፉባቸው መስኮች ከፍ ብለው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ እነዚህም ሆኑ እንደነርሱ ለስኬት ያልበቁ ሰዎች እኩል ከሚታዩባቸው ነገሮች አንዱ ለሕግ ተገዢ መሆን ነው፡፡ ለሕግ ተገዢ ከሚኮንባቸው ነገሮች አንዱ ደግሞ የታክስ ግዴታዎችን መወጣት ነው፡፡

በዚህ ረገድ በዓለማችንም ሆነ በሀገራችን ለታክስ ሕግ ተገዢ ሳይሆኑ የቀሩ በርካታ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት በሕግ ቁጥጥር ስር ውለው ምርመራ ከተደረገባቸው በኋላ የቅጣት ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት ከዓለማችን ታዋቂ ሰዎች መካከል የጥቂቶቹን የሕግ ጥሰት እና የተወሰደባቸውን እርምጃ እናቀርባለን፡፡

### ሲልቪዮ ቤርሉስኮኒ

ሲልቪዮ ቤርለስኮኒ፤ እ.ኤ.አ ከ1994 እስከ 2011 ጣልያንን ለሦስት ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት መርተዋል፡፡ ፎርብስ መጽሔት እ.ኤ.አ በ2009 ባወጣው መረጃ ከዓለማችን ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎች ቤርሎስኮኒ 12ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጠዋል፡፡ እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2014 ከዓለማችን ባለጸጎች ውስጥ በዘጠኝ ቢሊየን ዶላር ሀብት 141ኛ የዓለማችን ሀብታም ሰው ሆነዋል፡፡ በታዋቂው የጣልያኑ ኤሲሚላን እግር ኳስ ክለብና የሦስት ቴሌቪዥን ጣቢያዎች እንዲሁም የተለያዩ ድርጅቶች ባለቤት የሆኑት ቤርሎስኮኒ ሁሌም ከሚዲያዎች ትኩረት ጠፍተው የማያውቁ አነጋጋሪ ሰው ናቸው፡፡ በአንድ ወቅት ከወሲብ ቅሌት ጋር በታያያዘ «በሁለት ወር ውስጥ ከ33 ሴቶች ጋር ወስልተዋል» ተብለው ሲከሰሱ የሰጡት መልስ፣ "እኔ የ74 ዓመት አዛውንት ነኝ። 'ይወሰልታል' ብባል 33 ሴቶች በሁለት ወር ውስጥ እንኳን ለእኔ፤ ለ30 ዓመት ወጣትም እጅግ ብዙ ናቸው" በማለት ፈገግ የሚያሰኝ መልስ ሰጥተው ነበር፡፡

አብዝተው ስለራሳቸው መናገር የሚወዱት ቤርሎስኮኒ፣ በአንድ ወቅት፣ "የዓለማችን ምርጡ መሪ ነኝ እኔ" ብለው ነበር፡፡ ነገር ግን ሰውየው በምርጥ መሪነታቸው ሳይሆን አንዴ በታክስ ማጭበርበር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በወሲብ ቅሌት ከሚዲያዎች ዓይን ጠፍተው አያውቁም፡፡

ጣልያንን የምታክል ትልቅ አገር በጠቅላይ ሚኒስትርነት የመሩት ተጽእኖ ፈጣሪውና ባለጸጋው ሰው «ለአገራቸው መክፈል የነበረባቸውን ግብር አልከፈሉም» ተብለው ክስ ተመስርቶባቸው፡፡ ምክንያቱም ሰውየው «እንዲህ ዓይነት ቅሌት ይፈጽማሉ» ተብሎ አይገመትምና!

አንዳንድ ደጋፊዎቻቸው «ፓፒ ሲልቪዮ» ወይም "ሲልቪዮ አባታችን" ብለው ነበር የሚጠሯቸው፡፡ ምክንያታቸውም፤ «ቤርሎስኮኒ ሰው መርዳትና መስጠት የሚወዱ ቸር ሰው ናቸው» ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ ሰውየው ቸርነታቸው ለሴተኛ አዳሪና ከዕድሜ በታች ከሆኑ ሴቶች ጋር ለሚያደርጉት የወሲብ ቅሌት ነው እንጂ ለበጎ ተግባር አይደለም» በማለት ይከራከራሉ፡፡ የእነዚህ ወገኖች መከራከሪያ ነጥብ የሚያሳምን ይመስላል፡፡ ምክንያቱም፤ ቤርለስኮኒ «ካለው ለሌለው ማካፈል» የሚለውን የግብር/ታክስ ዓላማ ወይም መርህ ማክበር አልቻሉምና! እሳቸው በባለቤትነት የሚያስተዳድሯቸው ሦስት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ለመንግሥት መክፈል የነበረባቸውን አስር ሚሊየን ዩሮ ግብር ስላልከፈሉ ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

የጣልያን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ ኦገስት 1/2013 ዓ.ም በዋለው ችሎት ሲልቪዮ ቤርሎስኮኒ በተከሰሱበት የታክስ ማጭበርበር ወንጀል ጥፋተኛ መሆናቸውን አረጋግጧል፡፡ ቤርሎስኮኒ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩበት ጊዜ ስልጣናቸውን መከታ በማድረግ ለመንግሥት መክፈል የነበረባቸውን ግብር አልከፈሉም። ዓቃቤ ሕግ ያቀረባቸውን የሰው እና የሰነድ ማስረጃዎች በመመርመር ቤርሎስኮኒ ለፈጸሙት ወንጀል ሦስት ዓመት እስራት እና 10 ሚሊየንን ዩሮ ለመንግሥት እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡ ነገር ግን በጣልያን ሕግ መሰረት አንድ ከ70 ዓመት ዕድሜ በላይ የሆነ ግለ-ሰብ ወንጀል ፈጽሞ እስር ሲፈረድበት እስራቱ ወደ ማህበራዊ አገልግሎት ይቀየርለታል፡፡ በዚህ መሰረት ቤርሎስኮኒ ዕድሜያቸው 77 ዓመት በመሆኑ የእስራት ቅጣቱ ወደ ማህበራዊ አገልግሎት ተቀይሮላቸዋል። እናም፤ "ሳክራ ፋሚሺሊያ" በሚባል የአልዛይመር ህሙማን ማዕከል በሳምንት ለአራት ሰዓታት ማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል፡፡

አዲሱ የጣልያን የፀረ-ሙስና ሕግ ደግሞ አንድ ሰው ወንጀል ፈጽሞ ከሁለት ዓመት በላይ የሆነ እስራት ከተፈረደበት ለስድስት ዓመታት በማንኛውም የህዝብ ኃላፊነት እንዳይሳተፍ ያግዳል፡፡ በመሆኑም፤ የጣልያን ፓርላማ ቤርሎስኮኒ ከአባልነታቸው እንዲሁም ለስድስት ዓመታት በፓርቲያቸው /Forza Italia/ን ጨምሮ በማንኛውም የመንግሥት ኃላፊነት እንዳይሳተፉ እገዳ ጥሎባቸዋል፡፡ እርሳቸው ግን በቪዲዮ መልዕክት፣ «ባደገ ዓለም ሊደረግ የማይገባ በደል ነው በፍርድ ቤቱ የደረሰብኝ» ብለው ነበር፡፡

የማያስጥል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# በትግራይ ክልል የፌደራል ግብር ከፋዮች ልዩ አገልግሎት ሲሰጥ ነው

**በሰሎሞን ወርቁ**

በገቢዎች ሚኒስቴር የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ልዩ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ግብር ከፋዮች እየለየ መሆኑን ገለጸ።

በትግራይ ክልል የሰላም መደፍረስ በነበረበት ጊዜ ወደ ተቋሙ እየመጡ ግብራቸውን በወቅቱ እያሳወቁ፤ እንዳንዶቹም እየከፈሉ የነበሩ ግብር ከፋዮችን በልዩ አገልግሎት ለማስተናገድ የመረጃ ማጥራት ሥራ እየሠሩ መሆኑን የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ አቶ ተክላይ አብርሓ ተናግረዋል።

በጦርነቱ ወቅት በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሠራተኞች አገልግሎት መስጠታቸውን ባለማቋረጣቸው ግብር ከፋዮችም ቀርበው ግዴታቸውን ሲወጡ እንደነበር አስታውሰው ለእነዚህ ግብር ከፋዮች ልዩ እውቅና መስጠቱ ሌሎችም ወደዚህ አገልግሎት እንዲመጡ የሚያበረታታቸው እንደሚሆን ጠቁመዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ የፌደራል ተሞክሮን በመውሰድ በመቀሌ ዙሪያ የተጀመረ ዓመታዊ ሽያጫቸው 10 ሚሊዮን ብር እና ከዚያ በላይ የሆነው 350 ግብር ከፋዮች ለይተው ለብቻቸው አገልግሎት የሚያገኙበት አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ እየሠሩ መሆኑን የክልሉ ገቢዎች ቢሮ የሕግ ማስከበር ዳይሬክተር አቶ ተስፋዬ ታደሰ ተናግረዋል።

በዚህ አሠራር ከፍተኛ ግብር ከፋዮች በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በእቃዎች ክምችት እና ስርጭት እንዲሁም በደረሰኝ እና በሽየጭ መመዝገቢያ መሳሪያ ጉዳይ ላይ የተሻለ መረዳት እንዲኖራቸው የተሻሉ ባለሙያዎችን በመመደብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ከጦርነቱ በፊት በክልሉ አጠቃላይ 14ሺ ግብር ከፋዮች የነበሩ ሲሆን አሁን ትክክለኛ ቁጥራቸውን ለማወቅ ጥናት እያደረጉ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ስርዓት /system/ እስኪስተካከል ድረስ ሽያጮችን በእጅ በእጅ (በማንዋል) ደረሰኝ እንዲገበያዩ እያደረጉ እንደሆነም አስረድተዋል።

## ገቢዎችን የተመለከቱ ወቅታዊ፣ ትኩስ እና የተሟሉ መረጃዎችን ለማግኘት፡- በማህበራዊ መገናኛ ዘዴዎቻችን ይጎብኙ

1. በድረ ገጽ፡- www.mor.gov.e
2. በቴሌግራም፡- https://t.me/MoREthiopiaOfficial/169
3. በፌስቡክ፡- https://www.facebook.com/ERCA.info or ministryofrevenuesofethiopia /የገቢዎች ሚኒስቴር/
4. በዩትዩብ፡- https://www.youtube.com/@ministryofrevenuesofethiop1677/videos Or ministryofrevenuesofethiopia
5. በቲክቶክ አጫጭር መረጃ https://vm.tiktok.com/ZM61hdty2/

### በቴሌቪዥን ፕሮግራሞቻችን

6. ዋልታ ቴሌቪዥን ሰኞ ማታ ከ 2፡30 ጀምሮ
7. ፋና ቴሌቪዥን ሐሙስ ማታ ከ2፡00 ዜና በኃላ
8. ኢቲዮጵያ ቴሌቪዥን /ኢ.ቢ.ሲ/ ቅዳሜ ማታ ከ2፡00 ዜና በኋላ

### በሬድዮ ፕሮግራሞቻችን

9. ፋና ኤፍ ኤም ሬድዮ 98.1 ሐሙስ ማታ ከ2፡30 ጀምሮ
10. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬድዮ 93.1 ማክሰኞ ጠዋት ከ2፡30 ጀምሮ
11. በወርሃዊ ጋዜጣችን፡- ገቢያችን ህልውናችን

# ርዕሰ አንቀጽ



## ትውልድ ያስፍቅር፤ ሀገር ያስግብር

የሰው ልጅ የአዕምሮ ችግር ካልገጠመው በስተቀር ሀብታምም ይሁን ድሀ፤ የተማረም ይሁን ያልተማረ ወይም ሌላ፤ ዕድሜው ለአቅመ-አዳም ወይም ለአቅመ-ሔዋን ሲደርስ ፍቅር ሊይዘው ተፈጥሯዊ ግዴታው ነው፡፡ ይህ ጉዞው በፍቅር መነሻነት አስከ ትዳር ዘልቆ ራስን መተካት ደረጃ ይደርስና መኩሪያ እና መመኪያን ያጎናጽፋል፡፡

የትውልድ ፍቅሩ የትዳር አጋሩን አስገኝቶ ራስን መተካት ደረጃ ከማድረሱ ሌላ ሀገርም ላይ ይገለጻል፡፡ በዚህ ረገድ ሀገር ወዳድነት እስከ መስዋዕትነት የሚያደርሰው ወደ ፍቅር ደረጃ ሲደርስ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዜጎች በተለያዩ ወቅቶች ሀገር ላይ የውጪ ወረራ ሲካሔድ በከፈሉት መስዋዕትነት ዛሬ ያለችውን ሀገር ለትውልድ ማስረከባቸው መገለጫ አድርጎታል፡፡

ይህ የፍቅር መገለጫ ሰላም ኖረም አልኖረ የሚቀጥልባቸው ሌሎች መስኮችም አሉ፡፡ ከነዚህ አንዱ እና ዋነኛው ደግሞ ሀገር በራሷ አቅም እድገቷ የሚረጋገጥበትን ገቢ በግብር በመደገፍ ነው፡፡ ምክንያቱም፤ የሀገር እንደ ትውልድ በፍቅር መቀጠል ግብርም የምትከበርበት እና ራሷን እንድትችል የሚያደርጋት ስለሆነ፡፡

በኢትዮጵያ የግዛት ወሰን ውስጥ ለመኖር ማረጋገጫው የነዋሪነት መታወቂያ ወረቀት ወይም የዜግነት ማረጋገጫ ፓስፖርት መያዝ፣ ስለኢትዮጵያዊነት መዝፈን፣ መዘመር ወይም አብዝቶ መናገር መሆኑ ይታወቃል፡፡ እያንዳንዱ እንደዝንባሌው በተሰጠው የሥራ ኃላፊነት እና እንደተሰማራበት የሥራ መስክ የሚገባውን አገልግሎት ከሰጠ «ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልም» እንደተባለው ብቻ ሳይሆን የዜግነት ወይም የኢትዮጵያዊነት ድርሻውን መወጣቱን ያሳያል፡፡ እነዚህ ሁሉ ግን ብቻቸውን ሀገርን በሁለት እግሯ እንድትቆም ስለማያስችሉ በኢኮኖሚ አቅሟ እንድትጎለብት ዜጎች የአቅማቸውን ወይም ባገኙት ገቢ ልክ ተሰልቶ የሚጠበቅባቸውን ግብር መክፈል አለባቸው፡፡

ከአንድ አገር መሪ ጀምሮ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ምንጊዜም ስለወገኑ ማሰብ፣ መጨነቅ እና መሥራት አለበት፡፡ ኢትዮጵያን ኢትዮጵያ የሚያደርጋት ሕዝቦቿ በጋራ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት እና በመከባበር ሲኖሩ ብቻ ነው፡፡ መሪም እንደ መሪነቱ፣ ዲፕሎማት እንደ አገር ልዑክነቱ፣ ወታደር እንደ አገር ጠባቂነቱ፣ በፍትሕ ማስከበር ሥራ የተሰማራው እንደ ፍትሕ አስከባሪነቱ፣ የሚዲያ ባለሙያው እንደ ሙያ ሥነ-ምግባሩ፣ ፖለቲከኛውም እንደተሰጠው የሀገር አደራነቱ እንዲሁም ማንኛውም ዜጋ እንደሚጠበቅበት ተግባሩ የግብር ግዴታውን በመደበኛ ሥራውም ሆነ በትርፍ ጊዜ ወይም በግሉ በሚያገኘው ገቢ ላይ ተመርኩዞ ግብርን ሊከፍል ይገባዋል፡፡ ይህ ሲሆን ነው እንግዲህ ሀገር በግብር ገቢ አድጋ ከተመጽዋችነት እና ከተበዳሪነት መዝገብ የምትፋቀው፡፡ አለበለዚያ ግን በሀገራችን አሁን እየታየ ባለው የበጀት እጥረት የተነሳ በሀገር ውስጥ ግብር እና በወጪ ንግድ ቀረጥና ታክስ መተማመን የሚያስችለንን አቅም እርዳታ እና ብድርም ላይ እንድናተኩር ያደረገን አሠራር እንዲቀጥል ያደርገዋል፡፡ እርዳታ እና ብድር ደግሞ በለጋሽ እና በአበዳሪ ሀገራት እጅ ውስጥ ጥሎን የቅድመ-ሁኔታዎቻቸው ተገዢ እንደሚያደርጉን ባለፉት ዘመናት ስላየን ከጉዳቱ ተምረን ፍቅርንም፣ ግብርንም ከሀገራችን እኩል መስጠት ይገባል፡፡

ይህን አቋም የሚዲያ ተቋማትም ለሕዝቡ በማስተጋባት ኢትዮጵያዊ ተቆርቋሪነታቸውን ማሳየት አለባቸው፡፡ ከነዚህ አካላት በተጨማሪ በየትኛውም ጎራ የተሰለፉ ፖለቲከኞቻችንም ሆኑ አክቲቪስቶቻችን እንዲሁም የሃይማኖት አባቶች በየመድረኮቻቸው አስርጸው የሀገር ፍቅር ተጋሪነታቸውን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

«ከግብር እና ከሞት አይቀርም» አባባል ሰው ወድዶ እንደማይሞት ሁሉ ግብርም ወደድንም ጠላን የማይቀርልን ግዴታ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ፤ ዛሬ ባለመክፈል ነገ ከሚከሰት መጨናነቅ፣ መጠየቅ እና መቀጣት ለመዳን የግብር ሕግ ተገዢነታችንን ሁልጊዜ እያሰብን በተግባር እናውል፤ አውለንም ፍቅራችንን ለትውልድም፣ ለሀገርም እናሳይ፡፡

ገቢያችን ህልውናችን፤ በገቢዎች ሚኒስቴር የኮምዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የኤዲቶሪያል ቦርድ አባላት፡- አቶ አካሉ ጴጥሮስ ሰብሳቢ
አቶ እስክንድር መርሐጽድቅ አባል
አቶ ፀጥአርጋቸው ንጋቱ አባል

ዋና አዘጋጅ፡- እስክንድር መርሐጽድቅ
አዘጋጆች፡- ሺመልስ ሲሳይ
ሰሎሞን ወርቁ

ጸሐፊና ሌይአውት ዲዛይነር፡- ብርሃኔ ደመቀ
ፎቶግራፈር፡- ክፍሌ አዳፍሬ፣ እስካለም ሰፊው እና የትናየት እንዳያፍሩ

አድራሻ፡- ስልክ 11-6-17-84-90 ኮድ 8490 ፖ.ሣ.ቁ 2559
ዌብሳይት፡- www.mor.gov.et ኢሜል ethioerca@Gmail.com
ፌስቡክ Ministry of revenues of Ethiopia

ስታክስ እና ስጉምሩክ ጉዳዮች መረጃ ነጻ ስልክ፡- 8199

## ቃል በተግባር የተገለጸበት

በመላው ኢትዮጵያ ከሚገኙት የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ውስጥ በ180ዎቹ መካከል በታክስ እና በጉምሩክ ላይ የታኮረ የተማሪዎች ጥያቄና መልስ ውድድር ባለፈው ዓመት ተካሒዶ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት የመጨረሻዎቹ ዘጠኝ ት/ቤቶች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የማጠቃለያ ውድድራቸውን ሰኔ 24/2015 ዓ.ም. በስካይላይት ሆቴል አድርገው እንደየወጡበት ደረጃቸው ከላፕቶፕ እስከ ታብሌት እና ለውጤት ላበቋቸው መምህራን የገንዘብ ሽልማት ድረስ ተሰጥቶ ነበር፡፡

በዕለቱ በክብር እንግድነት የተገኙት ሚኒስትሯ እና ኮሚሽነሩ ለዘጠኙ ተማሪዎች እስከ ዩኒቨርሲቲ ማጠናቀቂያቸው ድረስ የትምህርት ወጪያቸውን ለመሸፈን ቃል መግባታቸው ይታወሳል፡፡

በዚሁ መሠረት ታኅሣሥ 5/2016 ዓ.ም. በስካይላይት ሆቴል ተካሒዶ በነበረው የፌዴራል እና የክልሎች የፋይናንስና ገቢዎች ዘርፍ ምክክር ጉባዔ ላይ ለእያንዳንዳቸው የ55ሺ ብር ሽልማት ሰጥተዋል፡፡ ድጋፉ በዚህ ሳይቆም ወደፊትም የሚቀጥል ሲሆን ይህ፤ ሚኒስቴሩ የገባውን ቃል በተግባር የሚፈጽም መሆኑን እንደሚያሳይ አመልካች ነው፡፡










እንግዳችን

አዘጋጅ፡- ሺመልስ ሲሳይ

# «የደረሰኝ አሰጣጥ ችግር የሚጀምረው ከአዲስ አበባ/መርካቶ ነው»

- አቶ ተክላይ አብርሓ

በሰለሞን ወርቁ



የገቢዎች ሚኒስቴር ለግብር ከፋዮቹ በተደራሽነት አገልግሎት የሚሰጥባቸው ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች 13 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ አምስቱ በአዲስ አበባ እና ስምንቱ ከአዲስ አበባ ውጪ ይገኛሉ፡፡ ከአዲ አበባ ውጪ ካሉት የመቀሌው ቅርንጫፍ አንዱ ነው።

በክልሉ ያሉ የፌደራል ግብር ከፋዮች የንግድ እንቅስቃሴ እና የግብር አከፋፈል ሁኔታ ምን እንደሚመስል ከገቢዎች ሚኒስቴር የመቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሥራ አስኪያጅ አቶ ተክላይ አብርሓ ጋር ቆይታ አድርገናል።

**የመቀሌ ገቢዎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ምን ያህል ግብር ከፋዮች አሉት?**

በሲግታክስ የምዝገባ ስርዓት መሰረት የፌደራል ግብር ከፋዮች 2ሺ 670 ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ፣ ዓመታዊ ትርፍ ግብር እንዲሁም ሌሎች ክፍያዎችን የሚከፍሉ 1ሺ 259 ግብር ከፋዮች ናቸው።

መጀመሪያ ላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር /TIN/ ወስደው ነገር ግን የንግድ ፈቃድ ሳያወጡ የቀሩ እንቅስቃሴ አልባ /inactive/ ግብር ከፋዮች በብዛት አሉ። ሌሎች ደግሞ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር፣ የንግድ ፈቃድም አውጥተው ሪፖርት ሳያደርጉ በዚያው የጠፉ፤ ነገር ግን በከፊል የንግድ እንቅስቃሴ ያላቸው /semiactive/ ግብር ከፋዮች አሉ። እንዲሁም ሌሎች በንግድ እንቅስቃሴያቸው ገቢ እንደሌላቸው /nill/ አሳውቀው በዚያው የሚጠፉ ግብር ከፋዮች አሉ። በመረጃ ማጥራት ኮሚቴ መሰረት 880 ግብር ከፋዮች ምንም ታሪክ የሌላቸው ሆነዋል። የንግድ ትርፋቸውን አሳውቀው እንዲከፍሉ የምንጠብቃቸው 1ሺ 559 ግብር ከፋዮች ሲሆኑ 1ሺ 259 ግብር ከፋዮች ደግሞ በሥራ ላይ ያሉ /active/ ሆነው የተገኙ ናቸው። በዚህም በኩል የተመዘጋቢዎችን ትክክለኛ ቁጥር ለማወቅ አሁንም እየሠራንበት ነው።

**በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የነበረው አገልግሎት አሰጣጥ ምን ይመስል ነበር?**

ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በደንበኞች አቀባበል እና መስተንግዶ እንዲሁም የግብር ከፋዮች የሕግ ማስከበር እና ማሳወቂያ ማቅረብ ላይ ሞዴል ተብሎ ነበር። ለዚህም በ2011 ዓ.ም በዋናው መ/ቤት የብር ዋንጫ ተሸላሚ፤ በ2012 ዓ.ም ብዙ ግብር ከፋዮችን ያሸለመ እንዲሁም በ2013 ዓ.ም ደግሞ በክልሉ ሞዴል የሚባል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነው።

**ግብር ከፋዮች ለቅርንጫፍ ጽ/ቤታችሁ በአብዛኛው የሚያቀርቧቸው ቅሬታዎች ምንድን ናቸው?**

ግብር ከፋዮች ከሚያነሷቸው ቅርታዎች አንዱ፣ ‹‹የወርሐዊ ግብራችንን ባንክ አስገብተን ለማሳወቅ ወደዚህ መ/ቤት እንመጣለን። የምንከፍለውም፣ የምናሳውቀውም እንዲሁም ደረሰኝ የምትሰጡንም በአንድ ስፍራ ላይ (በባንክ ወይም በዚሁ መ/ቤት በኩል) ኦንላይን ለምን አይሆንም? ለምንስ እንድንመላለስ እንገደዳለን? ሲስተማችሁን ሙሉ ብታደርጉት›› የሚል ነበር። አሁን ዋናው መ/ቤት በዚህ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ያለውን የኦንላይን ሥርዓት ወደ ሥራ ቢያስገባውም እኛ ገና የኢፋይሊንግ ጉዳይ ላይ ነን።

ሌላው፣ ‹‹የሲስተም መቆራረጥ ሲሆን በመብራትም ይሁን በሌላ ምክንያት ሲስተሙ ሲቋረጥ መልሶ ለመሥራት ጊዜ ይወስዳል። በመሆኑም የሲስተም አቅሙን ከፍ በማድረግ ከወረፋ ተላቀን አገልግሎቱንም ቶሎ ለምን አናገኝም?›› የሚል ነበር፡፡ ይህ ጥያቄ አሁንም ቀጥሏል።

ሦስተኛው ደግሞ የደረሰኝ ቁጥጥር ስርዓታችን ነበር። የታክስ ኦፕሬሽን ሥራዎች (በተለይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ኦፕሬሽን ሥራዎች) በመቀሌ ዙሪያ እንሠራ ነበር። የሕገ-ወጥ ደረሰኞችን ለይተን እርምጃ ለመውሰድ በምንሠራው ሥራ ወጥነት እንደሌለው የሚቀርብ አቤቱታ ነበር። ይህን የገለጹት፣ ‹‹አንዳንዶቹ ግብር ከፋዮች ላይ በተከታታይ መረጃ ይጣራል፤ እርምጃም ትወስዳላችሁ። ሌሎቹን ደግሞ ምንም ክትትል ሳይደረግባቸው እንዲሁ ተረስተው በዚያው ይቀራሉ፡፡ ስለዚህ ወጥነት ያለው ሥራ ብትሠሩ ጥሩ ነው›› በማለት ነው። በእርግጥ የደረሰኝ አሰጣጥ ችግር ከአዲስ አበባው መርካቶ የሚጀምር ሲሆን መቀሌ ከተማም ደረሰኝ ያለመቁረጥ እና ያለመስጠት ከፍተኛ ተግባራት አሉ።

ሌላው አሁን እየተነሳ ያለው ችግር የሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያ አጠቃቀም ላይ ሲሆን፣ ‹‹ስንገዛም፣ ስንሸጥም በሽያጭ መመዝገቢያ መሳሪያው ቢሆንም ወደ መሥሪያ ቤታችሁ ይዘን የምንመጣውን ደረሰኝ አንዳንድ ጊዜ ‹ፎርጅድ› ነው ትሉናላችሁ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መሳሪያው ከነጭራሹም አይሰጠንም፡፡ ስለዚህ፤ ሕገ-ወጥ የሆኑ ማሽኖች ካሉ እንዲወገዱ በትክክል ወደ ሥራ መግባት ያለባቸውን ደግሞ ተቆጣጥራችሁ ቆጥራችሁ አስገቡና ሁሉም ነጋዴ በደረሰኝ ስርዓት እንዲገበያይ ወይም ደግሞ የደረሰኝ ስርዓቱን ሙሉ በሙሉ የምትቀይሩበትን የአሠራር ስርዓት ይኑር›› የሚል ነው። ‹‹በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የምትሰጡትን አግልግሎት በክልሉ ባሉ ወረዳዎች እና ከተሞችም እንዲሰፋ ድጋፍ ብታደርጉልን›› የሚሉም አሉ።

**የሰው ኃይላችሁ ብዛት እና አያያዝ ምን ይመስላል?**

በአሁኑ ጊዜ በኮንትራት እና በቋሚነት የቀጠርናቸው ሠራተኞችን ጨምሮ 228 ናቸው። በ2016 ዓ.ም የሠራተኞችን የሥራ ተነሳሽነት ለማነቃቃት ከመቀሌ ዩንቨርሲቲ እና ከሌሎች አካላት ጋር በመተባበር የስነ-ልቦና እና ሌሎች የማነቃቂያ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል። ለሠራተኞች ያልተከፈለ የስምንት ወራት ደመወዝ ጥያቄ ለዋናው መሥሪያ ቤት ቀርቦ ጥሩ ደረጃ ላይ ስላለ የመጨረሻ ውሳኔውን እየጠበቅን ነው።

በ2015 ዓ.ም ለሠራተኞች ከብርድ ልብስ ጀምሮ ስኳር እና የመሳሰሉትን በማቅረብ ለአንድ ዙር ድጋፍ ተደርጓል። የትራንስፖርት ሰርቪስ አገልግሎቶችን በኪራይም እንዲሸፈን አድርገናል። በቅርቡ ደግሞ የሠራተኞች የካፌ አገልግሎት ሥራ ይጀምራል።

ህጻናት ልጅ ያላቸው ሠራተኞቻችን በተረጋጋ መልኩ ግብር ከፋዮችን እንዲያገለግሉ እስከ ሦስት ዓመት የሆናቸውን ህጻናት መንከባከቢያ (ማቆያ) አሟልተን አደራጅተናል። ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ 61 በመቶ ሴት ሠራተኞች 42ቱ ልጆቻቸውን በህጻናት ማቆያ ማዋል ስለሚፈልጉ በቂ ባይሆንም የህጻናት ተንከባካቢ ባለሙያዎች ቅጥር ፈጽመን ሥራ ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነን።



ግንባታው በመካሄድ ላይ የሚገኘው የመቀሌ ገቢዎች ቅ/ጽ/ቤት፤

**ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ እያስገነባ ያለው የቢሮ ህንጻ የአፈጻጸም ደረጃ ምን ያህል ነው?**

ሕንፃው ባለሁለት ምድር ቤት እና ባለስምንት ፎቅ /B2+G+8/ ሲሆን በ2012 ዓ.ም አጋማሽ ተጀምሮ በፍጥነት እየተገነባ እስከ ሦስተኛ ፎቅ ደርሶ በጦርነቱ ጊዜ ተቋርጦ ነበር። አሁን እንደገና እንዲጀመር ተቋራጩ ያቀረበውን የዋጋ ማሻሻያ መልስ እየጠበቀ ነው። ህንጻው ተገንብቶ ከተጠናቀቀ በኋላ አገልግሎት አሰጣጡ ለሠራተኞቻችንም፣ ለግብር ከፋዮችም ምቹ ይሆናል።

**ለግብር ከፋዮች የሚሰጡት ማሳሰቢያ ምንድነው?**

ግብር የማይቀር /ግዴታ/ በመሆኑ ለቅጣት እና ለወለድ ከመዳረግ እንዲሁም በክርክር ሂደት ጊዜን ከማባከን እና አላስፈላጊ ወጪን ከማውጣት በፊት የግብር ስርዓትን ማክበር ተገቢ ነው። በእርግጥ ባሳለፍናቸው ጊዜያት ሙሉ በሙሉ የግብር ተገዥነትን ለማክበርና ለማስከበር ችግር የነበረ ቢሆንም ከዚህ በኋላ ባሉት ጊዜያት ሕጋዊ ስርዓትን በመከተል መሥራት እንደሚያስፈልግ ሁሉም አካላት ሊያውቁት ይገባል።

# ለግንዛቤዎ

አዘጋጅ- ሰለሞን ወርቁ

# የታክስ ተመላሽ አገልግሎት

**ሀ) የገቢ ግብር ቅድመ ክፍያ ተመላሽ**

አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 50 (1) መሠረት ታክስ ከፋይ ሊከፍል ከሚገባው ታክስ በላይ የከፈለ ከሆነ ከተከፈለበት ቀን ጀምሮ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የተመላሽ ጥያቄውን መቅረብ አለበት፤
- በውጭ ኦዲተር የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ፤
- በሪፖርት ለሚታየው ተከፋይ ኦሪጅናል ሰነድ በታክስ/በግብር ዓይነቱ ለያይቶ ማቅረብ፤
- ግብር ለመከፈሉ የሚያሳዩ ኦሪጅናል የቅድመ ግብር ክፍያ ደረሰኝ እና ዲክላራሲዮን (የ2% እና የጉምሩክ ደረሰኝ 3% ማቅረብ)፤
- የቅድሚያ ግብር ክፍያ በዕቃ ግዥ ዋጋ ውስጥ ያለመካተቱን ወይም በተሰብሳቢ ሒሳብ (Accounts Receivable) መያዙን ማረጋገጥ፤
- በማንኛውም የግብር/የታክስ አይነቶች ላይ ዕዳ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት

**ለ) የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ የመደበኛ 15%**

**አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- የተመላሽ ጠያቂዎች ከማናቸውም ዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- ሊከፈል ከሚገባው ታክስ በላይ እንዲቀነስ የተደረገው ታክስ የሚከፈልበት ከሆነ የተጠቀሰው ታክስ ለቀጣዮቹ አምስት የሂሣብ ጊዜያት እንዲተላለፍ የተደረገ መሆኑ፤
- በብልጫ የተከፈለ ታክስ (ቀሪ ሂሣብ) መኖሩን የሚያረጋግጥ፣ ደጋፊ ኦሪጅናል የሂሳብ ሰነድ ማቅረብ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት፣

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

በዜሮ ምጣኔ

- በሥርዓቱ እንዲስተናገድ ከኢንደስትሪ ሚኒስቴር የተፈቀደለት መሆኑን ማረጋገጫ፤
- ታክስ ስለመከፈሉ የሚያረጋግጥ በግብር/በታክስ አይነቱ ኦሪጅናል ደጋፊ ሰነዶች፤
- የተመላሽ ጠያቂዎች ከማናቸውም ዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- Air Way Bill/cargo manifest (ማስጫኛ ፈቃድ)፤
- Bank Permit (Letter of Credit)፡፡ የተፋጠነ ስርዓት (ኤክሳይዝ ታክስን ጨምሮ)
- በሥርዓቱ እንዲስተናገድ ከኢንደስትሪ ሚኒስቴር የተፈቀደለት መሆኑ ማረጋገጫ፤
- ታክስ ስለመከፈሉ የሚያረጋግጥ በግብር/በታክስ አይነቱ ኦሪጅናል ደጋፊ ሰነዶች፤
- የተመላሽ ጠያቂዎች ከማናቸውም ዕዳ ነፃ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
- የአገር ውስጥ ግዥ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት ማቅረብ፤
- ከክልሎች የሚመጡ ከሆነ የሥራ ግብር ጡረታ የከፈለበት ክሊራንስ፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ሊኪዎች

- በአንድ የሂሳብ ጊዜ ከሚከናወን ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ውስጥ ቢያንስ 25% በዜሮ የማስከፈያ ልክ ታክስ የሚከፈልበት፣ በአገር ውስጥ አምራቾች ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርበውን ወርቅ ጭምር ቀሪ ሂሣብ መኖሩ የሚያረጋግጥ ደጋፊ የሂሳብ ሰነድ ማቅረብ፤
- ዕቃው/ አገልግሎቱ ወደ ውጭ ገበያ መላኩን/ መቅረቡን የሚያስረዳ ደጋፊ ሠነዶች (የግብይቱ ዋጋ ቢያንስ 25% መሆኑን የሚያረጋግጥ፣ የጉምሩክ ዱ/ን፣ የማስጫኛ የተከፈለ የባንክ ፈቃድ ደረሰኝ፣ ያስገኘው የውጭ ምንዛሪ ውል) አያይዞ ማቅረብ፤
- በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝና የድርሻ ስሌት የሚያመለክት ሠንጠረዥ፤

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**የባለ ልዩ መብት አገልግሎት**

- የዲፕሎማቲክና ኮንስለር ሚሲዮኖች እና ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እውቅና ማስረጃ፤
- የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በፍትሕ ሚኒስቴር የበጎ አድራጎት ኤጀንሲ እውቅና ማስረጃ፤
- ግብይት የተፈፀመበት የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ደረሰኝ፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት ሥራ ሂደት፣

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**በገዥው ተይዞ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክሰ**

- ግብይት የተፈፀመበት የተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ፤
- ደረሰኝ (ቫውቸር) ከመንግስት ተቋም የተሰጠ፤
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ወርሃዊ ማስታወቂያ፤
- በማናቸውም የግብር/የታክስ አይነቶች ላይ ዕዳ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡

አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሐ) በማዕድን /ነዳጅ ፍለጋ ሥራ ላይ የተሰማሩ ኩባንያዎች አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- በማዕድን/ነዳጅ ፍለጋ ሥራ ላይ የተሠማሩ ኩባንያዎች የታደሰ ያልተሰረዘ ፈቃድ፤
- የማዕድን ሚኒስቴር በሚያቀርበው ዝርዝር ውስጥ የተካተተ ኩባንያ ስለመሆኑ ማስረጃ (ግብይት የተፈፀመበት)፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**መ) ሌሎች በማናቸውም ሁኔታ የተከፈለ ብልጫ ክፍያ አገልግሎቱን ለማግኘት መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች**

- በማናቸውም ሁኔታ በብልጫ የተከፈለበት ተያያዥነት ያላቸው ማስረጃ፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት የሥራ ሂደት፣

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

Reverse Taxation

የቴክኒክ አገልግሎት ሰጪና ተቀባይ ውል፤

- የተሳሳተ ደረሰኝ መመለስ የተሳሳተውን ኦሪጅናል ደረሰኝ ማቅረብ፡፡

**አገልግሎቱ የሚሰጥባቸው ቦታዎች**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት የሥራ ሂደት

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**የታክስ ኦዲት አገልግሎት**

**ሀ) የሂሳብ መዝገብ ለሚይዙ ግብር ከፋዮች፣**

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- ኦዲት እንደሚደረግ ደብዳቤ እንደደረሰ የሂሳብ ሠነዶችን፣ መዝገቦችንና ማስረጃዎችን በሙሉ ማቅረብ፣
- በኦዲት ሂደት የተጓደለ ማስረጃዎችን ማሟላት፣
- የኦዲት ሥራው ሲጠቃለል፣ የኦዲት መግቢያና መውጫ ውይይት ላይ ቀንና ሰዓት አክብረው መገኘት፣
- ከመውጫ ውይይት በፊት የኦዲት ግኝቱን በዝርዝር ማወቅ፣
- በኦዲት መውጫ ቃለ-ጉባኤ ላይ አስተያየት መስጠት እና ተጨማሪ ማስረጃዎች ካለት ማቅረብ፣
- በኦዲት ግኝቱ ላይ ጥያቄዎች ማቅረብና ማብራሪያ ማግኘት፣
- የግብር እና ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ መቀበል፣
- በተቀጠረው ሰዓት መሠረት መገኘት፣

**አገልግሎቱ የሚሰትበት ቦታ**

- የታክስ ኦዲት ሥራ ሂደት፣

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ለ) የሂሰብ መዝገብ ለሚይዙ የንግድ ሥራን ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት፣ የንግድ ሥራው ንብረት ከ50% በላይ ለመሸጥ፣የተወሰነ የንግድ ዘርፍ / የማምረቻ ተቋም/ ቅርንጫፍ ለመሸጥ፣ ከአንድ በላይ ድርጅቶች ለመዋሃድ፣ ስም ለውጥ እና በአጠቃላይ ኦዲት ለሚስተናገድ የቅድመ ግብር ክፍያ ተመላሽ ለማድረግ፣**

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- የፀደቀ የባለአክስዮኖች ቃለ-ጉባኤ፣ (ድርጅትን ለመዝጋት ብቻ)፣
- ለኦዲት የሂሳብ ሰነዶች፣ መዝገቦችንና ማስረጃዎችን በሙለ ማቅረብ፣
- በኦዲት ሂደት ግብር ከፋዩ የተጓደለ ማስረጃዎችን ማሟላት፣
- የንግድ ሥራውን የሚያቋርጥ ማንኛውም ግብር ከፋይ የንግድ ሥራውን ካቋረጠበት ቀን ጀምሮ በ3 ቀናት ውስጥ ማስታወቅ፣
- የሂሳብ መግለጫዎችና አስፈላጊ መዛግብት፣ (ሙለ በሙለ የንግድ ሥራ ለመዝጋት ከሆነ) ለተቋረጠበት የግብር ዘመን በስልሣ ቀናት (60 ቀናት) ውስጥ አዘጋጅቶ ማቅረብ፣
- በሚቀርበው የሂሳብ መግለጫ መሠረት የሚፈለግበትን ግብር መክፈል፣
- የኦዲት ሥራው ሲጠቃለል፣ የኦዲት መውጫ ውይይት ላይ መገኘት፣
- ከመውጫ ውይይት በፊት የኦዲት ግኝቱን በዝርዝር ማቅረብ።

**አገልግሎቱ የሚሰትበት ቦታ**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት ሥራ ሂደት፣

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሐ/ ለንግድ ሥራ የተያዙ የተወሰኑ ካፒታል ንብረቶችን (ለንግድ፣ ለፋብሪካ፣ ለቢሮ የተያዙ ሕንፃዎች እና የኩባንያዎች አክሲዮን) በስጦታ ወይም በሽያጭ ለማስተላለፍ፣**

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- ለአክሲዮን/ለንግድ ሥራ ሕንፃ የተሸጠበትን ማስረጃ/ውል፣
- የንግድ ሥራ ሕንፃ ሽያጭ ከሆነ፣ የባለቤትነት ካርታ ኮፒ፣
- የንግድ ሥራው ሕንፃ የተገዛበትን ዋጋ እና እስከተሸጠበት ጊዜ የታሰበው የእርጅና ቅናሽ ከላልች ቀሪ ንብረቶች (ከአንድ በላይ ሕንፃ ላላቸው) ተለይቶ በዝርዝር አዘጋጅቶ ማቅረብ፣
- የሂሳብ መዝገብ ያልያዙ ግብር ከፋዮች ወይም ንብረቱ የግዥ ማስረጃ የሌላቸው ከሆኑ የቤት ሥራ ፈቃድ በተሰጠበት ጊዜ አግባብ ባለው መ/ቤት የተመዘገበ የቤቱ ዋጋ፣
- የንግድ ሥራው ቦታ/ሕንፃ/ ማምረቻ/ በሚመለከተው መ/ቤት በመሬት አስተዳዳር /በከተማ/ ወረዳ/ማዘጋጃ ቤት የቤቱ የዋጋ መረጃ፣
- የተወሰነውን ግብር እና ታክስ ስሌት ዝርዝር፣ የኦዲት መውጫ ውይይት ላይ መገኘት እና በኦዲት መውጫ ቃለ-ጉባኤ አስተያየት መስጠ፣
- ተጨማሪ ማስረጃዎች ካሉ ማቅረብ።

**አገልግሎቱ የሚሰትበት ቦታ**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት ሥራ ሂደት፣

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**መ/ የሂሳብ መዝገብ ለሚይዙ ግብር ከፋዮች ዴስክ ኦዲት ለማድረግ፣**

**አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች**

- ዴስክ ኦዲት እንደሚደረግ የደረሰ ደብዳቤ፣
- በደብዳቤ ላይ የተዘረዘሩትን መረጃዎችና ማስረጃዎች፣
- በዴስክ ኦዲት ሂደት የተጓደለ ማስረጃዎችን ማሟላት፣
- የኦዲት ሥራው ሲጠቃለል፣ የኦዲት መውጫ ውይይት ላይ መገኘት፣
- ከመውጫ ውይይት በፊት የኦዲት ግኝቱን በዝርዝር ከኦዲት የሥራ ሂደት ጠይቆ ማወቅ፣
- በኦዲት መውጫ ቃለ-ጉባኤ ላይ አስተያየት መስጠት እና ተጨማሪ ማስረጃዎች ካለ ማቅረብ፣
- በኦዲት ግኝቱ ላይ ጥያቄዎች ማቅረብና ማብራሪያ ማግኘት፣
- ዝርዝር የኦዲት ግኝት መረጃዎችን እና ግብር እና ታክስ ስሌት የተሠራበትን አሠራር ከኦዲት የሥራ ሂደት ጠይቆ ማግኘት፣
- የግብር እና ታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ መቀበል።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ተመላሽና አገልግሎት ኦዲት ስራ ሂደት/ቡድን/

አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

**ሠ/ በታክስ ውሣኔ ቅሬታ አጣሪ ጽ/ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው እና ውሳኔው የማስተካከያ የኦዲት ሥራ ካለው ይህን የኦዲት ሥራ ለማጠናቀቅ፣**

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- የጽ/ቤቱ ውሳኔ ከግብር ከፊዩ ማስረጃ ማቅረብ የሚጠይቅ ከሆነ ማስረጃዎችን በሙለ ማቅረብ፣
- የማስተካከያ የኦዲት ሥራው ሲጠቃለል የመውጫ ውይይት ላይ መገኘት፣
- በኦዲት መውጫ ቃለ-ጉባኤ ላይ አስተያየት መስጠት፣
- የተስተካከለ የግብር እና የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ መቀበል።

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ቦታ**

- የታክስ ኦዲት የሥራ ሂደት

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

ኢንቨስትጌሽን ኦዱት

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

**ረ/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየግብር ዘመኑ ልዩ ምርመራ ለሀገር ውስጥ ታክስ የኦዲት ሥራ፡-**

አገልግሎቱን ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች

- ኦዲት እንደሚደረግ ደብዳቤ እንደደረሰ የሂሳብ ሰነድችን፣ መዝገቦችንና ማስረጃዎችን በሙለ ማቅረብ፤
- የአዲት መውጫ ውይይት ላይ መገኘት እና በአዲት መውጫ ቃለ-ጉባኤ አስተያየት መስጠት፤

**አገልግሎቶቹ የሚሰጡባቸው ቦታዎች**

- በታክስ ማጭበርበር ምርመራ ዳይሬክቶሬት /የታክስ ማጭበርበር ምርመራ የሥራ ሂደት/

**አገልግሎቱ የሚሰጥበት ሁኔታ**

- በአካል በመገኘት፣ ህጉ በሚፈቅደው መሰረት በውክልና

# በየዓይነቱ






## የ150 ኪሎ ግራም ዱቄት ገንፎ

ጭላሎ ሚዲያ ሰሞኑን በአርሲ/በቆጂ ባካሔደው ስድስተኛው የገበሬዎች ፌስቲቫል ላይ በ150 ኪሎ ግራም የገብስ ዱቄት የተሠራ ገንፎን አሠርቶ ሺዎችን እንደመገበ አዘጋጁ ጋዜጠኛ አንዱዓለም ጌታቸው በፌስቡክ ገጹ አስነብቧል፡፡

ገንፎው ያካተታቸው፡-

150 ኪሎ ግራም የገብስ ዱቄት፤

15 ኪሎ ግራም ቅቤ፤

2 ኪሎ በርበሬ፤

2 ኪሎ ጨው፤

10 እስር እንጨት፤

5 ኩንታል ኩበት እና

200 ሊትር ውሃ ነው፡፡

ገንፎው፤ በ12 እናቶች ለስድስት ሠዓታት የተገነፋ ሲሆን ከተገነፋበት ወደ ፌስቲቫሉ ቦታ በመኪና ለማድረስ የ20 ደንዳና ወጣቶች ጉልበት ፈስሶበታል።

ባለፈው ዓመት በተመሳሳይ ፌስቲቫል 100 ኪሎ ግራም የገብስ ዱቄት የፈጀ ገንፎ ተሠርቶ የነበረ ሲሆን በቀጣዩ ዓመት ከዘንድሮው የጨመረ እንደሚሠራ አዘጋጁ አስታውቋል፡፡



## በእባብ መነደፍ

በዓለም ላይ ሦስት ሺ የእባብ ዝርያዎች ቢሆኑም በሰው ልጆች ላይ አደጋ የሚያደርሱት መርዘማዎቹ በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡

በእባብ መነደፋችንን በምን ማወቅ እንችላለን?

1. በተነደፈበት ቦታ ላይ ሁለት የንክሻ ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ፤

2. ቦታው ላይ የህመም ስሜት ይኖራል፤

3. እብጠት ይታያል፤

4. የመተንፈስ ችግር ይከሰታል፤

5. መጨነቅና አለመረጋጋት ይስተዋላል፡፡

ተገቢው የሕክምና እርዳታ እስኪገኝ መርዙ ቶሎ ወደ ሰውነት እንዳይሰራጭ፡-

1. የተጎዳውን ሰው እንዳይንቀሳቀስ ማድረግ፤

2. የተነደፈውን አካል ወደ ታች ዝቅ አድርጎ መያዝ፤

3. ቆዳውን ቶሎ በውሃ በሚገባ ማጠብ፤

4. ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ጨርቅ እየነከሩ የተነደፈው ቦታ ላይ ማኖር፤

5. የተጎዳው ሰው በቃሬዛ እንደተኛ ወደ ሕክምና መውሰድ፤

6. ተጎጂውን ማረጋጋት እና ወደ ህክምና ማእከል ማድረስ ይገባል፡፡

## የቅድሚያ ቅድሚያ

በሀገራችን ለትራፊክ አደጋ መከሰት ከዋነኞቹ መንስኤዎች አንዱ የአሽከርካሪዎች ለእግረኞች ቅድሚያ አለመስጠት ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የብዙዎች ሕይወት ተቀጥፏል፣ ለሕመም ተዳርጓል፣ ንብረትም ወድሟል፡ ፡ በቀጣዩ ፎቶ ላይ ከምትመለከቷቸው ተሽከርካሪዎች ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ ተመራመሩበት፡፡



# የማያስጥል ዝነኝነት ...

ከገጽ 1 የዞረ

### ዩልሪች ሆይሰን

ዩልሪች ሆይሰን፤ በባየር ሙኒክ፣ በጀርመን ብሔራዊ ቡድን እና በሀገሪቱ የእግር ኳስ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ ያላቸው ናቸው፡፡ የጀርመን የቀድሞዋ ፕዚዳንት አንጌላ ሜርክል የቅርብ ሰውም ነበሩ፡፡ በጀርመን ብሔራዊ እግር ኳስ ቡድን እ.ኤ.አ ከ1970 እስከ 1979 የግራ አጥቂ ስፍራ ተሰልፈው በአንድ የዓለም እና በሁለት የአውሮፓ ዋንጫዎች ጀርመንን ወክለው ተጫውተዋል፡፡ የ1974 ዓ.ም ዓለም ዋንጫ ምዕራብ ጀርመን ስታሸንፍ ዩልሪች ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል፡፡ በባየር ሙኒክ እግር ኳስ ክለብ በተጫዋትነት ዘመናቸው ስምንት ዋንጫዎች ሲያነሱ የክለቡ ፕሬዝዳንት ከሆኑ በኋላም ባየር ሙኒክ በዓለማችን ካሉ ዝነኛ ክለቦች አንዱ እና በአባለት ብዛት የመጀመሪያ እንዲሆን ካደረጉትም አንዱ ነበሩ፡፡

እ.ኤ.አ ኤፕሪል 20/2013 የጀርመን ብዙሃን መገናኛ በፊት ለፊት ገጻቸው ታዋቂው የባየር ሙኒክ የአግር ኳስ ክለብ ፕሬዝዳንት ዩልሪች ሆይሰን በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተከሰው ፍርድ ቤት መቅረባቸውን ዘግበው ነበር፡፡ እኚህ የ62 ዓመት አዛውንት «ብራስት ወረስት» የሚባል ጀርመን ውስጥ የሚገኝ አንድ ፋብሪካ ባለቤት ናቸው። ከዚህ ፋብሪካ ካገኙት ገቢ ለመንግሥት መክፈል የነበረባቸውን 3.5 ሚሊየን ዩሮ ግብር/ታክስ ባለመክፈላቸው ክስ ተመስርቶባቸው በሙኒክ ፍርድ ቤት ቀረቡ፡፡ ሆይስን በተመሰረተባቸው ክስ መልስ እንዲሰጡ ሲጠየቁ፣ «እውነት ነው፤ ለታክስ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት መክፈል የነበረብኝን ግብር አልከፈልኩም። እንዲያውም መክፈል የነበረብኝ 3.5 ሳይሆን 18.5 ሚሊየን ዩሮ ነው» አሉ፡፡ በወቅቱ በፍርድ ቤቱ ዙሪያ የነበሩት የሰውየው አድናቂዎችና ደጋፊዎች በሰሙት መልስ እጅግ ተደናግጠውና ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ ዓቃቤ ሕግ ግን፣ «ሆይሰን ሌላ ተጨማሪ መክፈል የነበረባቸው ግብር ሊኖር ይችላል» ብለው በመጠራጠር ሌላ ምርመራ ማካሄድ ጀመሩ፡፡ እውነትም ሆይሰን ለመንግሥት መክፈል የነበረባቸው እሳቸው እንዳሉት 18.5 ሳይሆን 28.5 ሚሊየንን ዩሮ መሆኑን የሚያሳይ አንድ ሰነድ በቤታቸው ያገኛሉ፡፡ ዓቃቤ ሕግም ክሱን አሻሽሎ «28.5 ሚሊየን ዩሮ» በሚል ክስ አቀረበ፡፡

ብዙ ጊዜ እንዲህ ዓይነት የታክስ ወንጀል ሲሠራ በአንድ ሰው ብቻ ሊሆን እንደማይችል የታወቀ ነው፡፡ ሆይሰንም ይህን ሁሉ ወንጀል ሲፈጽሙ ተባባሪ ነበራቸው፡፡ ስለዚህ በፋብሪካቸው አማካኝነት እ.ኤ.አ ከ2004 እስከ 2009 ከሌላ አገር ያገኙትን ገቢ በስዊዝ ባንክ ሚስጥራዊ አካውንት በማዘጋጀት ገንዘቡን ሲያስተላልፍላቸው የነበረው አንድ የባንክ ሠራተኛ ነው፡፡ መርማሪዎች፤ ግለሰቡ በቁጥጥር ውሎ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ በጠየቁት መሰረት በፖላንድ ዋርሶ ከተማ ተይዞ ምርመራ ሲካሔድ ትክክለኛነቱ ተረጋገጠ፡፡



ዩልሪች ሆይሰን ፍርድ ቤት ቀርበው ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት እንዳለ ሲጠየቁ፣ "በሕይወቴ ትልቁን ስህተት የፈጸምኩት መክፍል የነበረብኝን ግብር ላለመክፈል የሠራሁት ስህተት ነው። ለዚህም ከቤተሰቦቼ ጋር ተመካክሬ ፍርድ ቤቱ የሚጥልብኝን ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፤ ለጠበቆቼም ይህንን እንዳይቃወሙ ነግሬያቸዋለሁ" በማለት የተሰማቸው ፀፀት ገልጸው ነበር።

ጉዳዩን ሲመረምር የቆየው የሙኒክ ፍርድ ቤት እ.ኤ.አ ማርች 13/2013 በዋለው ችሎት ለፈፀሙት ወንጀል ተመጣጣኝ ነው ያለውን ሦስት ዓመት ከስድስት ወር እስራት ወስኖባቸዋል፡፡



### ዋልተር አንደርሰን

በአሜሪካ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የገቢ ግብር ባለመክፈል ወደር ያልተገኘለት ሰው ዋልተር አንደርሰን ነው፡፡ አንደርሰን በአሜሪካ የቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ የተሰማራ ባለሀብት ሲሆን ከዚህ ኢንቨስትመንት ካገኘው ትርፍ ለአገሩ መክፈል ኖሮበት ያልከፈለው 183 ሚሊዮን 779ሺ 618 የአሜሪካ ዶላር ነው።

ግለሰቡ እ.ኤ.አ ከ1995 እስከ 1999 ከዚህ ዘርፍ የሚያገኘው ገቢ ለአሜሪካ ፌደራል አገር ውስጥ ገቢ አገልግሎትና ለኮሎምቢያ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት አሳውቆ ግብር ባለመክፈሉ በዓቃቤ ህግ ክስ ተመስርቶበት ፍርድ ቤት ቢቀርብም የቀረበበትን ክስ «ውሸት ነው» በማለት ተከራክሯል፡፡

ስለዚህ፤ «እኔ ንጹህ ሰው ስለሆንኩ በዚህ ወንጀል ልከሰስ አይገባም» አለ፡፡ መርማሪዎች ግን መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በሌላ ሰው ስም እና አገር ያስቀመጠውን የባንክ ደብተር ኮፒ ለፍርድ ቤቱ አቀረቡ፡፡ ፍርድ ቤቱም የሁለቱንም ወገኖች ክርክር እና ዓቃቤ ሕግ ያቀረበውን የሰውና ሰነድ ምስክሮች መርምሮ አንደርሰን ለመንግሥት መክፈል የነበረበትን ግብር ባለመክፈሉ ጥፋተኛ መሆኑን አረጋገጠ፡፡ በመሆኑም መክፈል የነበረበት ግብር 183 ሚሊየን 779ሺ 618 የአሜሪካ ዶላር እንደተጠበቀ ሆኖ 75 በመቶ ወለድ እና ቅጣት ተጨምሮበት በድምሩ 253 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ለመንግሥት እንዲከፍል እና በዘጠኝ ዓመት እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

**ይቀጥላል...**

# Fame does not ...

Continued from page 7

file income tax returns for six consecutive years and avoiding $7 million in taxes. He claimed he was following the advice of tax advisors who said he wasn't legally required to pay taxes. His advisor turned out to be wrong, and Snipes was sentenced to four years in prison, serving 24 months.

**Martha Stewart**

In addition to her high-profile conviction for insider trading, television personality and entrepreneur Martha Stewart was fined $221,677 for unpaid New York state taxes on her home in the Hamptons.



**Leona Helmsley**

Leona Helmsley and her husband, Harry, were indicted on 188 counts of tax fraud by then-U.S. Attorney Rudy Giuliani in 1988. The couple owned a $5 billion hotel empire. While both of the Helmsleys were charged, Harry was found mentally and physically unfit to stand trial due to his poor health and deteriorating mental condition. That left Leona to face the tax evasion charges alone.

In 1992, 71-year-old Leona was found guilty of 33 felonies. She was initially sentenced to 16 years in prison, fined $7.1 million, and ordered to do 750 hours of community service. However, the prison sentence was reduced to four years on appeal, and she ended up serving only 21 months.

Have Questions About Tax Crimes? Talk to a Lawyer

Failing to file or pay taxes can have serious consequences. There may be a fine line between legal tax avoidance techniques and unlawful tax evasion. As you can see from the famous examples shown above, it is important to understand what happens if you go too far. If you have tax questions or received a notice from a tax agency, it's a good idea to contact an experienced tax attorney to discuss your situation and find out about your options moving forward.

Source :- J.P. Finet, J.D. | Legally reviewed by J.P. Finet, J.D. | Last reviewed November 09, 2023

# የታክስ ኦዲት የሚደረጉ ...

ከገጽ 8 የዞረ

ሆን ተብሎ ሕገ-ወጥ አሠራር ሊኖር ይችላል። ሌላው፤ ትክክለኛ ባልሆነ እና በተጭበረበረ መረጃ እንዲሁም በተመላሽ ስም ከመንግሥት ቋት ለመውሰድ ቅድመ-ታክስ ቫት ተመላሽን መጠየቅ አለ፡፡ ለዚህም ማስተማር ዋናው ሥራ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ኪሳራን አጋንኖ ማምጣት ወይም ተገቢ ያልሆነ ኪሳራ ማሳወቅ ይታያል፡፡ በዚህ መልኩ በ2013 ዓ.ም በኦዲት 51 ቢሊዮን ብር ተገኝቷል፡፡ በ2014 ዓ.ም 29 ቢሊዮን ሲሆን በ2015 ዓ.ም ደግሞ ቀንሷል፡፡ ለዚህም ማስተማሩ ግብር ከፋዮችን እንዲጠነቀቁ አድርጓቸዋል፡፡

የማጭበርበር ሥራዎችን ከፍትሐ ብሔር በተጨማሪ በወንጀልም እንዲጠየቁ እየተደረገ ነው፡፡ ለምሳሌ፤ ማከማቻ ውስጥ ዕቃ ሳይኖር የተፈቀደላቸውን ደረሰኝ ብቻ በመጠቀም ወጪን አጋንኖ ማምጣት፣ በሃሰተኛ ማንነት ፍቃድ በማውጣት ደረሰኝ አሳትሞ ብቻ መሸጥ ወይም በሌሉ ሰዎች ፈቃድ አውጥቶ መሥራት ስለሚታይ እነዚህን ለይተን እናወጣለን፡፡ እነዚህን የወንጀል ጉዳዮች የኢተለጀንስ እና የምርመራ ዳይሬክቶሬት ክፍልም ይሠራበታል፡፡

የታክስ ኦዲት የሥራ ክፍል ገቢ የሚጎዱ ነገሮችን መከላከል ኪሳራ ተጋንኖ የመጣ እንደሆነ የማስተካከል ትምህርት የመስጠት ሥራዎችን ይሠራል፡፡ ታክስ ከፋዮችም ይህንን አውቀው እና ተጠንቅቀው ግብራቸውን በማሳወቅ እና በመክፈል ገቢን ከፍ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፡፡

አንድ ኦዲተር ውሳኔን የሚያሳልፈው በመሥሪያ ቤቱ የአሠራር ሥርዓት እና ማንዋል መሰረት ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ችግር ሲታይበት በመሥሪያ ቤቱ የሥነ-ምግባር መመሪያ ቁጥር 6/55 (7) መሰረት ይጠየቃል። ኦዲት ከሚደረገው ድርጅት ጋር የጥቅም ግጭት (የዝምድናም ይሁን ውግንና) አለመኖሩን ቃለ-መሃላ ይፈጽማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኦዲተሮች የግብር ከፋዮችን ምስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለባቸው። ኦዲት በሂደት የሚሠራ የቡድን ሥራ በመሆኑ አንዱ ቢሳሳት ሌላው ያርመዋል።

አንዳንድ ጊዜ በድርጅቱ እና በኦዲተሩ በኩል የጥቅም ፍላጎት ይታያል። በዚህ ጉዳይ የተጠረጠረ አንድ ባለሙያ በመኖሩ እየተጣራበት ይገኛል።

የተፈቀደላቸው የግል የሂሳብ አዋቂዎች ከሚያቀርቡት የታክስ ሥርዓት ጋር ያልታረቀ ሪፖርት ኃላፊነት እና ተጠያቂነት አለባቸው፡፡ ለባንክ (ለብድር) የሚቀርበው የሂሳብ ዝርዝር /financial ሪፖርት/ እና ለገቢዎች ሚኒስቴር የሚቀርበው የሂሳብ ዝርዝር /financial ሪፖርት/ መለያየት የለበትም፡፡ እነዚህ የተፈቀደላቸው ኦዲተሮች ያረጋገጡትን መረጃ ከአንድ የመረጃ ቋት ማግኘት ተገቢ ቢሆንም ይህንንም የሚያደርገው እስካሁን የኦዲት ኮርፖሬሽን ብቻ ነው፡፡ ሌሎቹ ግን ኃላፊነት ቢኖርባቸውም እያደረጉ አይደለም፡፡ ስለዚህም መረጃዎችን ከባንክ ለማግኘት እንዲቻል በትብብር ለመስራት ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

# Concerning tax ...

Continued from page 7

The other duty that is expected from the taxpayer is notifying the tax. The taxpayer has to notify its tax using the timetable set by the Ministry. This will be accomplished electronically without having to visit the office.

3. Reporting: -

The taxpayer who notifies his tax has to present the relevant documents that validates his tax amount. The documents are income statement, balance sheet and cash flow.

4. Paying the tax: -

This is the fourth step that the tax payer is expected to fulfill. The tax payer is expected to pay his tax voluntarily according to the time table set by the ministry.

# Tips

BY SHIMELIS SISAY

# Fame does not save from accountability

people can be seen well-known in many fields like film, music, journalism, arts, sports, politics, business and other popular fields. Law observance is something that both successful and unsuccessful people share. One of the most important aspects of obeying the law is tax compliance.

In this regard, many people in in the world as well as our country who are not willing to obey the tax law have been investigated and sentenced at different times. In this regard, many persons in our country and around the world who refuse to obey the tax law have been investigated and jailed at various times.

Accordingly, we present the rule violations of some of the world's most renowned persons, as well as the actions taken against them.



**Walter Anderson**

An American entrepreneur, Walter Anderson made his millions after the breakup of AT&T in 1984. He was convicted of the largest tax evasion case in U.S. history for evading more than $200 million in taxes. It was reported that in 1998, he paid $495 in taxes on $67,939 of income. The IRS alleged he made at least $126 million that year, hiding the income using offshore corporations. Anderson was sentenced to nine years in federal prison.





**Richard Hatch**

America was watching in 2000 as Richard Hatch received $1 million for winning the first year of the reality TV show "Survivor." CBS sent the IRS and Hatch Forms 1099 reporting those winnings. However, he failed to pay taxes on that income and other earnings from his new celebrity status. In 2006, Hatch was convicted of tax evasion in federal court and served a 51-month prison sentence as a result. Hatch returned to prison for nine more months after he failed to amend his 2000 and 2001 returns.



**Ron Mix**

Ron Mix was a Hall-of-Fame offensive lineman with the San Diego Chargers who became a successful workers' compensation lawyer after his playing career ended. He pleaded guilty to reporting $155,000 in referral fee payments as charitable donations between 2010 and 2013 and paid a fine of nearly $50,000.

**Willie Nelson**

Willie Nelson was a household name for having written and performed such country music standards as "On the Road Again" and "Whisky River" when he



began his decades-long struggle with the IRS over unpaid taxes in the 1990s. The federal government ended up seizing most of Nelson's property to pay his reported $32 million tax liability. It's believed that his tax woes were the result of bad advice he received from an accountant who hid Nelson's money in bogus tax shelters.

In the end, Nelson negotiated a settlement with the IRS. and recorded The IRS Tapes: Who'll Buy My Memories? as part of the settlement to pay down his tax debt. The IRS only collected $3.6 million from sales of the album, but Nelson's career eventually picked up and he paid off the rest of his debt.



**Al Capone**

Alphonse **Gabriel** Capone was an infamous Chicago gangster in the early Twentieth Century who was linked to murder, extortion, and bootlegging. He was eventually brought down for tax evasion after prosecutors failed to make any other charge stick. In 1931, Capone received an 11-year sentence for not paying $215,000 in taxes. He did not serve the full term and retired in Florida.



**Paul Daugerdas**

In a case dubbed by federal prosecutors as the biggest criminal tax fraud in history, former attorney Paul Daugerdas received a 15-year prison sentence and was ordered to forfeit $165 million for helping his clients evade taxes. He was convicted of creating a fraudulent tax shelter that would claim fictional losses to reduce the tax bills of the extremely wealthy. During its operation, the tax shelter generated more than $7 billion in fraudulent losses, resulting in $1.6 billion in lost tax revenue.



**Wesley Snipes**

Wesley Snipes received a three-year prison sentence for willfully failing to

Continued on page 6

## The standing committee evaluate the ministry's performance

At the Federal democratic republic of Ethiopia parliament; the standing committee of plan, budget and finance has evaluated the four-month performance of the Ministry of revenues.

At the occasion, the chairman of the committee his honorable Mr. Desalegn Wedaje, stated that the ministry is doing encouraging activities to boost tax compliance by building internal partnerships, which have a favorable impact on assuring sustainable revenue.

His honorable Abraham Alemayehu (Ph.D.), the deputy chairperson of the committee on his side said that, it is critical to take action against unlawful traders who refuse to provide a receipt.

Ms. Aynalem Niggusie, Minister of revenues, stated that the ministry has collected more income than as compared to the plan in the last four months. According to her, this revenue came from domestic revenue and customs duty.

## Concerning tax compliance

Tax compliance means following to the regulations, guidelines, and tax laws enacted by governments in order to collect taxes and customs properly.

Every taxpayer will be anticipated to fulfill the following four basic conditions.

1. Registering as a taxpayer;
2. Announcing their tax promptly;
3. Reporting the accurate tax;
4. Paying tax;

1. Taxpayer registration: -

Every individual and institution that is engaged in any business activity will be required to register as a taxpayer. This should be done on a voluntary and personal initiation. To be tax compliant, registering for all types of taxes is mandatory.

The main prerequisites for registering as a taxpayer in Ethiopia are to provide fingerprints, obtain a taxpayer identification number, and keep a record.

2. Notifying the tax: -

Continued on page 6

# ሕግ-ግብር

አዘጋጅ:- ስሎሞን ወርቁ


# የታክስ ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶች እና መስፈርቶቹ



አቶ ብርሃኑ አበበ የታክስ ኦዲት ዳይሬክተር፤

በኢትዮጵያ የግብር አከፋፈል ሥርዓት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም ማለት ግብር ከፋዮች ሠርተው፤ ገቢና ወጪያቸውን አስልተው በማሳወቅ ካተረፉት ለአገር መሰረተ-ልማቶች ግንባታ የሚሆንን ክፍያ የሚከፍሉበት ነው። ይህ መብትም ግዴታም የሆነ አሠራር የሚመራበት የሕግ ማዕቀፍ እንዳለው በመግለጽ ተያያዥ የሆነ ማብራሪያን የሰጡት የሚኒስቴሩ የታክስ ኦዲት ዳይሬክተር አቶ ብርሐኑ አበበ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የምትከተላቸው ዓለም አቀፋዊ የሒሳብ መርሆዎች የሚመሩት በሕግ ማዕቀፍ ሲሆን ብዙ የታክስ ዓይነቶችም በዚህ የሕግ ማዕቀፍ ይመራሉ፡፡ ግብር ከፋዮች እነዚህን የታክስ ዓይነቶች እና የሚከፍሉትን የታክስ መጠን ለይተው እንዲያውቁ በንግድ ሥራቸው ወይም በተለያዩ ሥራዎች ላይ ያገኙትን ገቢ እና ያወጡትን ወጪ ለይተው መመዝገብ ይገባቸዋል። በመዘገቡት የገቢ እና የወጪ ልዩነት መሰረት ከትርፉ ላይ የሚከፍሉትን የግብር መጠን ለግብር ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት በማሳዎቅ መክፈል ይገባቸዋል። ግብር ከፋዮች ይህን ለማድረግ የሚከተሏቸው የተለያዩ የታክስ እና የገቢ አስተዳደር አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪዎች እና አንዳንድ ጊዜ ለአፈጻጸም እንዲመች በሚል የሚወጡ ወቅታዊ ደብዳቤዎችን መሰረት በማድረግ ነው።

በእነዚህ የሕግ ማዕቀፎች መሰረት ግብር ከፋዮች በሕግ ተገዥነት መሰረት የተሰጣቸውን ኃላፊነት እና መብት በአግባቡ ተጠቅመው መሥራት አለመሥራታቸው የሚረጋገጥበት ትልቁ መሳሪያ የታክስ ኦዲት ነው፡፡

በገቢዎች ሚኒስቴር የታክስ ኦዲት ዳይሬክቶሬት ሦስት የሥራ ክፍሎች አሉት። አንደኛው የታክስ ኦዲት /brain minded/ የሚባለው ሲሆን ይህ የሥራ ክፍል የታክስ የአሠራር ሥርዓቶችን፣ ደረጃዎችን እንዲሁም አደረጃጀትንም ጭምር የሚቀርጽ እና የወጡትን የአሠራር ሥርዓቶች በአግባቡ መተግበራቸውን የሚከታተል ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በመጀመሪያው የተዘረጋውን የአሠራር ሥርዓት ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን /standards/ በመከተል በዕቅድ፣ በአፈጻጸም እና በማጠቃለያ ሪፖርት ደረጃ ምን ይሠራል የሚለውን መርሆዎችን የሚከተል ነው፡፡ ሦስተኛው አደረጃጀት ዓለም አቀፍ የታክስ እና የዋጋ ትልልፍን የሚከታተል ነው። ይህ ቡድን ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ የተዋቀረ ሲሆን ዝምድና ወይም ልዩ ግንኙነት ያላቸው ነጋዴዎች እርስ በእርስ የሚያደርጉት ግብይት የገቢን ዋጋ መሰረት ደረገ መሆን አለመሆኑን ይመረምራል፡፡ ይህንን በተመለከተ አሁን አሁን ከUK እና ከHMRC ጋር በመተባበር እየተሠራ ነው፡፡

የታክስ ኦዲት የሚደረጉ ድርጅቶች የሚለዩት የግብር አከፋፈል የስጋት ደረጃን መሰረት ያደረገ ሲሆን ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ ያሉ ተብለው ይለያሉ። በፌደራል ደረጃ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ኦዲት ማድረግ የሰው ኃይል፣ የገንዘብ እና የጊዜ እንዲሁም የመሰረተ ልማቶች /logistice/ አለመሟላት ስላለ የግብር ከፋዮችን የስጋት ደረጃ ለመለየት በ22 መስፈርቶች መሰረት ቅድሚያ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ ላይ ያሉትን ኦዲት በማድረግ ይሰራል። ይህ አሠራርም ከሰው አወንታዊም እና አሉታዊም ሀሳብ ነጻ የሆነ ሲሆን መረጃዎችን ለኮምፒውተር ሲስተም በመመገብ / feed በማድረግ/ አማካይ ውጤቱን ይገልጻል። በዚህ መረጃ መሰረት የድርጅቶቹ የስጋት ደረጃ የሚያይ ይሆናል እንጂ ሰዎች በዘፈቀደ የሚያደርጉት አሠራር አይደለም።

በስጋት እና የሕግ ተገዥነት ስትራቴጂ ዳይሬክቶሬት በኩል የድርጅቶች ስጋት ደረጃ ተጣርቶና ተለይቶ ከተቀመጠ በኋላ ድርጅቶች/ግብር ከፋዮች በከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ተለይተው ወደ ታክስ ኦዲት ዳሬክቶሬት ይቀርባሉ፡፡

በዚህ መሰረት በ2015 ዓ.ም በገቢዎች ሚኒስቴር በአጠቃላይ ከተመዘገቡት 60ሺ ግብር ከፋዮች ውስጥ 30ሺ 578 ግብር ከፋዮች/ድርጅቶች ኦዲት እንዲደረጉ ለዳይሬክቶሬቱ ቀርበዋል። በዚህ መሰረት ከ30ሺ 578 ውስጥ 8154 ወይም 28 በመቶ ግብር ከፋዮችን ብቻ ተደራሽ አድርጓል፡፡ ይህንንም ከፍተኛ ስጋት ካለባቸው ወደ መካከለኛ፤ ከዚያም ወደ ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ እየመጣ ዓመቱ እስኪያልቅ ድረስ ከደረሰበት ይቆማል፡፡

ይህ አሠራር በ13ቱም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሚሠራበት ሲሆን ግብር ከፋዮች የኦዲት አሠራርን በተመለከተ ክትትል የሚደረገው ግብራቸውን በሚከፍሉበት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ነው፡፡ በዋናው መ/ቤት ደግሞ ስትራቴጂክ ሥራዎችን ይሠራል፡፡ ድርጅቶች ኦዲት ሲደረጉ ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የአሠራር ውስብስብነት ያለባቸው ሊሆኑ ይችላሉ። ለዚህም ከፍተኛ፣ መካከለኛ እና ጀማሪ የኦዲት ባለሙያዎችን በመመደብ ሥራው እንዲሠራ ይደረጋል።

አንድ ድርጅት ኦዲት እንዲደረግ በ15 ቀናት ውስጥ መረጃውን አሟልቶ በማቅረብ በተቀመጠለት ጊዜ ውስጥ ኦዲት ተደርጎ መጠናቀቅ አለበት፡፡ ግብር ከፋዮች/ድርጅቶች ኦዲት ሊደረጉ ሲፈለግ እና መረጃዎች እንዲቀርቡ ሲጠየቁ ሁሉንም መረጃዎች አሟልተው ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡ ፡ መረጃቸውን ይዞው ሲቀርቡ የመግቢያ ስብሰባ በማድረግ ድርጅቱ የት ቦታ እንደሚሠራ፣ ያሉትን ሀብቶች፣ አሠራር ሥርዓቱ፣ የባንክ አካውንቶቹ፣ የግብይቱ ሰንሰለት ምን እንደሆነ ቃለ-መጠይቅ ተደርጎ ይያዛል፡፡ መረጃዎቹን መሰረት በማድረግ ተቀባይነት ያገኙ ወይም ያጡ እና ወደ ውሳኔ የሚመጡ ተብለው በመለየት ከባለሙያዎች ጋር በመግባባት ይሠራል። በውሳኔው ላይ ከድርጅቱ አመራሮች ወይም ባለሙያዎች ጋር የመውጫ ስብሰባ በማድረግ ይጠቃለላል። ውሳኔ ከወጣበት በኋላ መረጃዎችን ማምጣት እና ለማስተካከል መሯሯጥ ብዙውን ጊዜ ወጪ ማብዛት ነው የሚሆነው።

በዚህ አሠራርም መግባባት የማይኖር ወይም ስህተት የሚታይበት ከሆነ የታክስ ኦዲት የቁጥጥር ሥርዓት በየቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ባሉ ባለሙያዎች የሚሠራ ሲሆን በዋናው መሥሪያ ቤትም የሚሠራ ነው፡፡ ታክስ ከፋዩች የሚያነሷቸውን ጉዳዮች ከሕግ፣ ከሒሳብ መርሆዎች እና ከመረጃዎች አንጻር በደንብ ማየት፣ መመርመር እና ውሳኔ ማሳለፍ ያስፈልጋል፡፡

ከዚህም በኋላ አጠቃላይ ኦዲት ከተደረጉት ድርጅቶች/ግብር ከፋዮች ውስጥ ናሙና በመውሰድ እና በመመርመር ትክክል መሠራት አለመሠራቱን የሚያረጋግጥ የታክስ ኦዲት ጥራት ማረጋገጫ የሥራ ክፍል በ2015 ዓ.ም ኦዲት ከተደረጉት 353 በትክክለኛው ሥርዓት ማለፋቸውን በመመልከት ለይቷል። በዚህም ባለሙያዎች በስህተት ካለፉ ወይም አለአግባብ በግብር ከፋዮች ላይ ጫና ፈጥረው ከሆነ በአፈጻጸም ሂደት የመረጃ መጓደል ወይም በሥነ-ምግባር ጥሰት የአመራር ጉድለት መሆኑን ይመረምራል፡፡ ቀጥሎም ጣልቃ በመግባት ችግሩ የሥነ-ምግባር፣ የአቅም ጉዳይ እና ጉልህነት ያለው ስህተት ከሆነ እንዴት ይታረማል የሚለውን ማጠቃለያ ይሰጣል፡፡ በመጨረሻም፤ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 85 መሰረት የሚወስነው የበላይ ኃላፊ እንዲወሰንበት የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል። በዚህ ላይ ገቢ ቀርቶ ከሆነ እንዲመጣ ማድረግ፣ በግብር ከፋዩ ላይ ኢ-ፍትሃዊ ሆነ ውሳኔ ተሰጥቶ ከሆነ ማስተካከል ይሆናል፡፡

የኦዲት ግኝትን በተመለከተ ኦዲቱም፣ ታክስ ከፋዮችም 50 በመቶ ትክክል ናቸው ብሎ መነሳት አለበት፡፡ የአሠራር ሥርዓትና ሕግን በውል አለማወቅ እና አለመጠቀም ወይም

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ኢትዮጵያ በየወሩ 19 ሚሊየን ዶላር ታጣለች



ከኢትዮጵያ በሕገ-ወጥ መንገድ ከሀገር በሚወጡ የቁም እንስሳት የተነሳ በየቀኑ ከ630ሺ ዶላር በላይ እንደምታጣ ተገለፀ። ይህ ሀገሪቱን ከዚህ ሕገ-ወጥ ንግድ ብቻ በወር 19 ሚሊየን እና በዓመት 229 ሚሊየን 950ሺ ዶላር በላይ ያሳጣታል፡፡

ይህ ተገለጸው በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት አዘጋጅነት ሕገ-ወጥ ንግድን መከላከል ላይ ያተኮረ ሀገር አቀፍ ጉባዔ ሲካሔድ ነው። ምክር ቤቱ በዚሁ ጊዜ ሕገ-ወጥ ንግድ በስፋት በሚታይባቸው ዘርፎች ላይ ያካሄዳቸውን ጥናቶች ይፋ አድርጓል።

ጥናቶቹ እንዳመለከቱት፤ ሕገ-ወጥነቱ በቁም እንስሳት፣ በመድኃኒት፣ በጨርቃጨርቅ እና በሎጂስቲክስ ሥርዓትም ላይ ታይቷል። በቁም እንስሳት ኤክስፖርት ግብይት ላይ የሚታዩ ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳቦችን በተመለከተ ጥናት ያቀረቡት በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንተርፕራይዝ ልማት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አለባቸው ንጉሴ ናቸው።

በሕገ-ወጥ ንግዱ ምክንያት ባለፉት ስምንት ዓመታት ከቁም እንስሳት ንግድ የሚገኘው የውጭ ምንዛሬ እየቀነሰ መምጣቱን ጠቅሰው ቀደም ሲል ከዘርፉ እስከ 150 ሚሊየን ዶላር የሚጠጋ ገቢ ይገኝበት የነበረው በ2014 ዓ.ም እና በ2015 ዓ.ም. ወደ 17 ሚሊየን ዶላር መውረዱን አስረድተዋል።

የችግሩ ምንጭም የሕገ-ወጥ ንግድ ስልትና ዓይነት እየተቀያየረ መምጣቱ፣ የክትትልና የቁጥጥር ሥራው አጥጋቢ አለመሆኑ እንዲሁም በቴክኖሎጂ የተደገፈና ሕጉን የጠበቀ የግብይት ሥርዓትን ማስተግበር ላይ ክፍተቶች መኖራቸው ነው ብለዋል። እንዲሁም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የቁም እንስሳት ልየታና ከተቀባይ አገራት ጋር ያለው ሕጋዊ ስምምነት ላይም ክፍተቶች እንደሚታዩ ማንሳታቸውን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዘገባ አመልክቷል።

**የገቢዎች ሚኒስቴር ራዕይ**

በ2022 ዘመናዊ የታክስ አስተዳደር ተገንብቶ ሀገራዊ ወጪ በታክስ ገቢ ተሸፍኖ ማየት

**እ ሴ ቶ ች**

1. አገልጋይነት (Customer centric)
2. ሙያዊ ብቃት (Professionalism)
3. በቡድን መሥራት (Team work)
4. መሰጠት (Dedication/commitment)
5. ታማኝነት (Loyality)